Seattle Public Utilities

### አፓርትመንትና ኮንደሚንየም

# ምግብ እና ብስባሽ

**በቆሻሻ መጣያ ወይም የሪሳይክሊንግ ሳጥኖች ውስጥ ምግብ መጣል ክልክል ነው**

**እነዚህን ነገሮች በምግብና በጓሮ ጥራጊ መጣያ ውስጥ ይጨምሩ**

## የምግብ ትርፍራፊ


ፍራፍሬ


አታክልቶች


የተፈጨ ቡናና ማጥለያዎች


የሻይ ኮሮጆዎች


ዛጎሎችና አጥንቶች


ፓስታና ሩዝ


የእንቁላል ቅራፊና የኦቾሎኒ ገለባ


ዳቦና ጥራጥሬ እህል


ስጋ፣ ዓሳ እና የወተት ውጤት

## ምግብ የነከካው ወረቀት


የወረቀት ኮሮጆዎች፣ የወረቀት ፎጣዎች እና ናፕኪኖች


ቅባት የነካው የፒሳ ባኮ


ምግብ የነካካው በኬሚካል የተቀባ ወረቀት


የተቆራረጠ ወረቀት (ከጓሮ ጥራጊ ጋራ ይቀላቅሉ)



ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ ኮሮጆዎች

## የአታክልትና የጓሮ ጥራጊ


አበቦችና የቤት ውስጥ ተክሎች


ቅጠላ ቅጠሎች፣ ቅርንጫፎችና የታጨደ ሳር

**ላስቲክ ክልክል ነው።**
**የላስቲክ ቦርሳዎች ክልክል ናቸው።**
**ብረት ክልክል ነው። ጠርሙስ ክልክል ነው።**
**የእንስሳ ዓይነ ምድር ክልክል ነው።**

## የምግብ ትርፍራፊ ለምን ያጠራቅማሉ?

**ብክነትን ይቀንሱ፤** የሲያትል ነዋሪዎች ሲሶው ቆሻሻ የምግብ ትርፍራፊ ነው። ወደ ጉድጓድ ውስጥ እንዲሞላ ከመላክ ፈንታ፣ በአካባቢው ውስጥ በሚገኙ መናፈሻ ቦታዎችና የአበባ መደቦች ውስጥ ያለውን አፈር ለማዳበር ወደሚረዳ ብስባሽ ይቀይሩት።

**መልከዓ ምድሩ፤** በሚጣልበት ጉድጓድ ውስጥ የምግብ ትርፍራፊ ሜቴይን ያመነጫል— ከ CO2 22 ጊዜ እጥፍ የበረታ የግሪንሃውስ ጋዝ። የምግብ ትርፍራፊን በጠራቀሚያው ሳጥን ውስጥ በመጨመር የአየር ንብረታችንን ይጠብቁ።

**ዋጋው፤** ከፍተኛ ወጪዎችና የተደፈኑ የፍሳሽ ቱቦዎች እንዳይኖሩ ይከላከሉ። የምግብ ትርፍራፊን በምግብ ትርፍራፊ ማጠራቀሚያዎ ውስጥ ይጨምሩ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ፈንታ። ይህ ደግሞ ውሃንና ሀይልን ይቆጥባል!

**ሕግ ነው፤** በከተማው ሕግ መሰረት፣ የምግብ ትራፊ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ክልክል ነው። የምግብ ትራፊና የጓሮ ጥራጊ ማጠራቀሚያ ሳጥን ለነዋሪዎች መቅረብ ይኖርበታል።



### ጥያቄዎች
### ሳጥኑ ውስጥ ምን ማግባት ይችላል?

**የጋርደን ሆትላየን ስልክ ቁጥርን ይደውሉ**
**(206) 633-0224**
**ወይም ይጎብኙ**
**www.seattle.gov/util/foodwaste**

ስለ ኩሽና ምክሮች በሌላ ገጽ ይገኛሉ ▶



# የማጠራቀሚያ ምክሮች

**ጥሩ ነገር ለምን ይባክን?**

በሲያትል የሚገኙ ሁሉም መኖሪያ ቤቶች የምግብ ትራፊና የጓሮ ጥራጊ መሰብሰቢያ አገልግሎቶች አሏቸው። የምግብ ትራፊና የጓሮ ጥራጊ ከማጠራቀሚያ ሳጥኖች በየሳምንቱ ይሰበሰባሉ። የኩሽና የምግብ ትራፊዎችን ለመሰብሰብ ቀላል የሚያደርጉ ምክሮች እነዚህ ናቸው፤



## በኮሮጆ ውስጥ ይጨምሩት

የምግብ ትርፍራፊን ለማጠራቀም፣ ቡናማ የወረቀት ኮሮጆን ወይም ወደ ብስባሽ ሊቀየር የሚችል የተፈቀደ ኮሮጆን ይጠቀሙ።
የሞላውን ኮሮጆ በምግብ ትራፊና የጓሮ ጥራጊ ማጠራቀሚያ ሳጥን ውስጥ ይጣሉ። ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ የሚፈቀዱ ኮሮጆዎችን ለማግኘት በ **www.seattle.gov/util/foodwaste** ይመልከቱ። እንዲሁም በአካባቢዎ ብዙ ሱቆች ውስጥ ይገኛል።



## ያጠራቅሙት

የምግብ ትርፍራፊን ለማጠራቀም፣ ክዳኑ በደምብ የሚገጥም ማጠራቀምያ ይጠቀሙ። እውስጡ ያሉትን አውጥተው ይድፉ ወደ ምግብ ትራፊና የጓሮ ጥራጊ ማጠራቀሚያ ሳጥን ውስጥ፣ ከዚያም አለቅልቀው ማጠራቀሚያውን እንደገና ይጠቀሙበት።



## ጋዜጣውን ይጠቀሙበት

የምግብ ትርፍራፊን በጋዜጣ ጠቅልለው ወደ ሳጥኑ ይጣሉ።

## ያቀዝቅዙት

የምግብ ትርፍራፊን ኮሮጆ ውስጥ ይጨምሩ ወይም ይጠቅልሉ። ከዚያ በኋላ ማጠራቀሚያ ሳጥን ውስጥ እስከሚጥሉ ድረስ ፍርጅ ወይም ፍሪዘር ውስጥ ያስቀምጡ።

## ይክደኑት

በማጠራቀሚያ ሳጥኑ ውስጥ፣ ያለውን የምግብ ትርፍራፊ ምግብ በነካካው ወረቀት፣ የተቆራረጡ ወረቀት፣ ጋዜጣ፣ ወይም በጓሮ ጥራጊ ሽታንና ተባዮችን ለመከላከል ይሸፍኑ።

**የላስቲክ ኮሮጆዎች ማጠራቀሚያ ሳጥን ውስጥ አይፈቀዱም — ብስባሹን ያበላሹታል።**



የተፈቀዱ
ወደ ብስባሽ ሊቀየሩ የሚችሉ
የኮሮጆ ማሸጊያ
የተሰራ
ከአታክልት

For interpretation services, please call 206-684-3000.
如需要口譯服務，請撥電話號碼 206-684-3000.
통역 서비스를 원하시면 206-684-3000 으로 전화하세요.
Wixii turjubaan afka ah ku saabsan, Fadlan la soo xariir taleefoonka: 206-684-3000.
Para servicios de interpretación por favor llame al 206-684-3000.
Para sa serbisyo ng tagapagpaliwanag, tumawag sa 206-684-3000.
Về dịck vụ phiên dịch xin gọi 206-684-3000.

Seattle Public Utilities
WASTE MANAGEMENT Think Green.
Recology CleanScapes WASTE ZERO

www.seattle.gov/util 206-684-3000 TTY 206-233-7241

AM